**የቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞ ክራሲ ድጋፍ ሰጭ በኩቤክ ።**

**Support group of CUD in Quebec.**

**skinijit@yahoo.com**

ጥር ፡ ፫ ፡ ቀን ፡ ፳፻ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፤

“በፊት ፡ ነበረ ፡ እንጂ ፡ አልሞ ፡ መደቆስ ፣
አሁን ፡ ምን ፡ ያደርጋል ፡ ወጭት ፡ ጥዶ ፡ ማልቀስ” ፤ ይሏችኋል ፡ እንደ ፡ እነዚህ ፡ እና ፡ እንደ ፡ እነዚያ ፡ ያሉትን ፡ ነው ።

ይድረስ ፡ ለአፈንጋጭና ፡ አከፋፋይ ፡ አንጃወች ፤

በታኅሣሥ ፡ ፴ ፡ ቀን ፡ ፳፻ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ ባስተላለፍነው ፡ የድጋፍ ፡ መልእክት ፡ ቅር ፡ እንደ ፡ ተሰኛችሁ ፡ የሰደባችሁንን ፡ በደስታ ፡ አንብበነዋል ። “ምቀኛ ፡ አታሳጣኝ” ፡ ነውና ፡ ያበሳጫችሁ ፡ መሠረት ፡ ያለውን ፡ ነክተናል ፡ ማለት ፡ ነው ። እና ፡ የተከበሩት ፡ አቶ ፡ በድሩ ፡ አደም ፣ “አፍንጫየን ፡ እስካልመታችሁኝ ፡ ድረስ ፡ የፈለጋችሁትን ፡ ጥያቄ ፡ ጠይቁኝ” ፡ ያሉትን ፡ ቃል ፡ ተውሰን ፣ እኛንም ፡ አፍንጫችንን ፡ እስካልመታችሁን ፡ ድረስ ፡ ስድቡ ፡ ስለማይጣበቅብን ፡ አራግፈነዋል ። በተቀዳሚ ፡ እንድታውቁልን ፡ የምንፈልገው ፡ ግን ፣ መሪያችንን ፡ በሚገባ ፡ ስለምናወቃቸው ፡ ስለ ፡ እርሳቸው ፡ ባሕርይና ፡ አሠራር ፡ አትንገሩን ። ቀንታችሁ ፡ ከሆነና ፡ አስተማሪ ፡ መሪ ፡ ከሌላችሁ ፡ ደግሞ ፣ ንሥሐ ፡ ግቡና ፡ “በማወቅም ፡ ሆነ ፡ ባለማወቅ ፡ በሠራችሁት ፡ ኃጢያት ፡ እግዚአብሔር ፡ ይፍታችሁ” ፡ ተብላችሁ ፡ ልትሠሩ ፡ ትችላላችሁ ። ለኢትዮጵያዊነታችሁ ፡ በተግባር ፡ ካስመሰከራችሁ ፡ እኮ ፡ ወገኖቻችንን ፡ እንወዳችኋለን ።

የቅንጅትን ፡ መሥራችና ፡ መሪ ፡ በዚያና ፡ በዚህ ፡ ግዜ ፡ ያነንና ፡ ይኸን ፡ አድርጓል ። እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ባሕርይ ፡ አለው ። በዚያ ፡ ዘመን ፡ በነፃ ፡ ትምህርት ፡ የተማሩት ፡ እንደነዚያ ፡ እንደነዚያ ፡ ያሉት ፡ ናቸው ። የመሳሰለውን ፡ ጠቅሳችሁልናል ። የማታውቁትን ፡ ከመዘባጠር ፡ ይልቅ ፡ ስለ ፡ እምታውቋቸው ፡ አለቆቻችሁ ፡ ለምን ፡ ማውራት ፡ አስጠላችሁ? ። አልታወቃችሁም ፡ እንጂ ፡ እኛ ፡ እኮ ፡ በዓይኖቻችን ፡ ዓይተን ፣ በጆሮዎቃችን ፡ አዳምጠን ፡ ማመዛዘን ፡ የምንችል ፡ አገርና ፡ ወገን ፡ ወዳድ ፡ ኢትዮጵያውያኖች ፡ ነን ። እናም ፡ ስለ ፡ ተከበሩት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ተወካይ ፡ መሪያችን ፡ በማስረጃ ፡ አጥንታችሁ ፡ ያገኛችሁት ፡ ሳይሆን ፡ እርሳቸውም ፡ ተናግረውታልና ፡ አበጁ ። እኛም ፡ ስለ ፡ እርሳቸው ፡ “በጥቂቱ ፡ ቆንጥረን” ፡ እንናገር ፡ ነበረ ፡ ያልን ። እንጂ ፡ ስለ ፡ እርሳቸው ፡ ለመጻፍ ፡ አልነበረም ። ቢሆንማ ፡ ኖሮ ፡ በአንድ ፡ ሺህ ፡ ገጽ ፡ እንኳ ፡ አንመለስም ፡ ነበረ ። አሁንም ፡ “በድንጋይ ፡ ላይ ፡ ውሃ ፡ ማፍሰስ” ፡ ባይሆንብን ፣ የትግሉ ፡ ዓላማ ፡ ስለ ፡ ክቡር ፡ ኃይሉ ፡ ሻውል ፡ አይደለም ። ስለ ፡ እናት ፡ ኢትዮጵያና ፡ ሕዝቧ ፡ ነውና ፡ ለቀቅ ፡ አድርጉ

ን ። እኛ ፡ ለምንደክም ፡ ምን ፡ አስጨነቃችሁ? ። እናንተም ፡ መብታችን ፡ ነው ፡ ለምትሉበት ፡ ቀጥሉ ። የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ እንደሆነ ፡ የሚያደርገውን ፡ አውቆ ፡ ይወስናል ።

በሌላ ፡ አቅጣጫ ፡ ደግሞ ፣ ክቡር ፡ መኃንዲስ ፡ ኃይሉ ፡ ሻውል ፡ ተምረው ፡ የሚያስተምሩ ፣ ታግለው ፡ የሚያታግሉ ፡ ናቸው ። የሕዝብ ፡ ተወካይ ፡ በመሆን ፡ ለእናት ፡ አገራቸውና ፡ ሕዝቧ ፡ እስተ ፡ መጨረሻው ፡ ሕይወታቸው ፡ ሕዝብን ፡ ለማንቃት ፡ ቆርጠው ፡ የተነሡ ፡ መሆናቸውን ፡ ተናግረውታል ። ለምን ፡ ንግግር ፡ ከሚያደርጉበት ፡ ሄዳችሁ ፡ የፈለጋችሁትን ፡ ጥያቄ ፡ አትጠይቋቸውም? ።

እኛ ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ የምንኖር ፡ ደጋፊዎቻቸው ፡ እንጂ ፡ እርሳቸው ፡ ስለ ፡ እኔ ፡ ተናገሩልኝ ፡ ብለው ፡ የተወከልን ፡ አይደለንም ። በጣም ፡ የሚገርመው ፣ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ዐሥራ ፡ ሰባት ፡ ዓመት ፡ ሙሉ ፡ ያለ ፡ መሪ ፡ እራሱን ፡ ችሎ ፡ እያስተዳደረ ፡ እንደሆነ ፡ እንኳ ፡ መገንዘብ ፡ የተሳናችሁ ፡ ምን ፡ ዓይነትስ ፡ ፍጡሮች ፡ ብትሆኑ ፡ ነው? ። ያችን ፡ የመሰለች ፡ አገር ፡ በውጭ ፡ የልመና ፡ ገንዘብ ፡ እስተ ፡ መቼ ፡ የምትለማ ፡ መስሎ ፡ ታይተችኋል? ። የወገኖቻችን ፡ መሰቃየትስ ፡ አያሳስባችሁም? ። ዋሽቶና ፡ እንቅልፍ ፡ አጥቶ ፡ ከመቸገር ፣ እውነቱን ፡ ይዞ ፡ ተኝቶ ፡ ማደር ፡ አይሻላችሁም? ። ይህችን ፡ አጭር ፡ ጽሑፍ ፡ ስናዘጋጅ ፣ እኛን ፡ ለመሰሉም ፡ዐውቀው ፡ እንዲጠነቀቋችሁ ፡ በማሠብ ፡ ጭምር ፡ ነው ።

**በአምላኳ ፡ እርዳታና ፡ በልጆቿ ፡ ብርታት ፡ ኢትዮጵያ ፡ ታሸንፋለች!! ። በክቡር ፡ መኃንዲስ ፡ ኃይሉ ፡ ሻውል ፡ መሪነት ፡ ከቅንጅት ፡ ጋራ ፡ ወደፊት!!! ።**

**ከቅንጅት ፡ ደጋፊዎች ፣**
**ኩቤክ ፣ ካናዳ ።**